የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAG.03.24/12/4
ቀን 01/09/2015

ለተከበሩ ዶ/ር ቢቂላ ሁሪሳ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የህዝብ ግኙኙነትና ኮሚኒኬሽን ከፍተኛ አማካሪ እና

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የቦርድ ሰብሳቢ

ለክቡር አቶ ሰይፈ ደርቤ

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የ2014 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤትና አስተያየት በቁጥር OFAG.03.24/12/25 በቀን 29/06/2015 መላካችን ይታወቃል፡፡ሆኖም የኦዲት ሪፖርቱ ከተላከላችሁ በኋላ ተጨማሪ ማስረጃ ያቀረባችሁ በመሆኑም የቀረበው ማስረጃ ታይቶ የተስተካከለ የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 10 ገጽ ኦዲት ሪፖርት እና 10 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች በድምሩ 20 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ጌታሁን [illegible]
የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

Office of the Federal Auditor General

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት
ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት /2015

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ
ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የመንግስት የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣

• የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው።

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች፡-

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የ2014 የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በኮሚሽኑ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

<u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች(Emphasise Matters)</u>

1. <u>በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝግብና በሂሳብ ሪፖርት ላይ ልዩነት የታዩ የገቢ ሂሳብ</u>

   የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን እና ሪፖርት መመዝገብና ማቅረብ እንዳለባቸው መመሪያው ይገልጻል:: ይሁን እንጂ በአገልግሎቱ በሰኔ 30/2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 1451199 ብር 21,782,725.47 የገቢ ሂሳብ የሚታይ ሲሆን በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ብር 21,791,127.47 ተመዝግቦ የሚታይ በመሆኑ የበጀት ዓመቱ የገቢ ሂሳብ ሪፖርት በብር 8,400.00 በማነስ ሪፖርት ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

2. <u>ያለአግባብ የተፈጸመ የመብራት ክፍያ</u>

   የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤት ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል:: በዚህም መሰረት አገልግሎቱ የመንግስትን መመሪያዎች በተሟላ መለኩ ስራ ላይ

ማዋሉንና የተመደበለትን በጀት ከብክነት ጠብቆ እያስተዳደረ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

የአገልግሎቱን አዲስ ህንፃ ግንባታ ስራ እያከናወነ የሚገኘው ይርጋለም ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ የተጠቀመበትን የመብራት ፍጆታ በድርጅቱ መሸፈን ሲገባው በቀን 30/10/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 10899 በሂሳብ መደብ 2241101 ብር 201,112.78 ያለአግባብ ከአገልግሎቱ ክፍያ በመፈጸሙ የወጪ ሂሳብ ከፍ ብሎ እንዲታይ ያደረገው መሆኑ፤

3. <u>ከሁለተኛው አሸናፊ በተጋነነ ዋጋ ያለ አግባብ የተፈጸመ ግዥ ክፍያ በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ 2002 አንቀፅ16.19.3 በአሸናፊዉ ተጫራች የቀረበዉ ዋጋ ጨረታዉ ከመዉጣቱ በፊት በመንግስት መ/ቤቱ ከተገመተዉ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ልዩነት የሚበልጥ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ባለመሆኑ አዲስ ጨረታ ማዉጣት የሚሻል መሆኑ ሲታመንበት ድጋሚ ጨረታ ማዉጣት አስፈላጊ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ የዚህን መመሪያ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደርግ፤
አገልግሎት መ/ቤቱ 2014 በጀት አመት ለተቋሙ አገልግሎት የሚውል፡-

- የተለያዩ ኬብሎችና ኮኔክተሮች ግዥ ለመግዛት ታህሳስ 04/2014 ተጠይቆ በወጣዉ የዋጋ ማወዳደርያ ኒርታጅ አስመጭ በድምር ብር 121,000.00 ዋጋ በመስጠት ያሸነፈ ቢሆንም ድርጅቱ በወቅቱ እቃዎቹ እስቶር ውስጥ የሉኝም በማለቱ በሚል ከሁለተኛው አሸናፊ ሐም ሚዲያ ቴክኖሎጂ በድምር ብር 211,114.00 ግዥው በማከናወን በልዩነት በብር 90,114.00 ክፍያ ተፈጸመ መሆኑ፡
- የኦምኒ ዳይሬክሽናል ማይክ ለመግዛት የካቲት 02/2014 ተጠይቆ በወጣዉ የዋጋ ማወዳደርያ ኒርታጅ አስመጭ ብር 81,000.00 ያቀረበና ያሸነፈ ቢሆንም ድርጅቱ በወቅቱ እቃዎቹ እስቶር ውስጥ የሉኝም በማለቱ በሚል ከሁለተኛው አሸናፊ ሐም ሚዲያ ቴክኖሎጂ ብር 126,011.00 ግዥ በማከናወን በልዩነት ብር 45,011.ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- የበር ስራ ግዥ በዋጋ ማወዳደርያ ይህኤል ጠ/የመስታወት ስራ በብር 120,419.26 ያሸነፈ ሲሆን ድርጅቱ ስራዉን ለመስራት ፍቃደኛ ባለመሆኑ በሚል ከሁለተኛው አሸናፊ ከፀጋ ኢንጂነሪግ በብር 217,799.00 ግዥው በመፈጸም ከመጀመሪያው አቅራቢ በልዩነት ብር 97,379.74 ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ፡

በአጠቃላይ በሁለቱ አቅራቢዎች መካከል ያለውን ከፍተኛ ልዩነት ስለሆነ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ለማወቅ ጥናት ማድረግ ወይም በድጋሚ ሌላ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ የመንግስትን ጥቅም ማስከበር ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ አቅርበው በሁለተኛነት ካሸነፉት ድርጅቶች ግዥ በመፈፀሙ በድምር ብር 232,504.74 አለአግባብ መንግስትን ለወጪ የዳረገ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

4. <u>በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጸደቀ ተመን ሳይኖር የተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ፤</u>

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት እንደገና ለማቋቋም በወጣ አዋጅ 1115/2011 ለሚሰጣቸው አገልግሎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚጸድቅ ደንብ መሠረት ክፍያ ማስከፈል እንዳለበት ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር190/2002 ስለ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ክፍል 4.21.1 የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያቀርቡት አገልግሎት አዲስ ተመን ወይም በነባር ዋጋ ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስትሩ በኩል ለሚኒስቴሮች ም/ቤት አቅርበው ማጽደቅ እንደሚኖርባቸው ይገልጻል፡፡ -

ይሁን እንጂ አልግሎቱ ከሚሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 22,502,347.99 የተሰበሰበ ቢሆንም በደንቡ መሰረት የክፍያ ተመን በማዘጋጀት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ በማፀደቅ ገቢውን መሰብሰብ ሲገባው ያለተመን ከአገልግሎት ክፍያ ገቢ እየሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡የጸደቀ የገቢ ማስከፈያ ተመን ወይም ታሪፍ ከሌለ የተሰበሰበው ገቢ መሰብሰብ በሚገባው ልክ መሆኑን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

5. <u>ያለሂሳብ አርዕስቱ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ይገልጻል ፡፡ አገልግሎቱ የወጪ ሂሳቦችን በትክክለኛው የሂሳብ አርዕስታቸው እየመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ የወጪ ሂሳቦች

ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡- በድምሩ ብር 913,488.25 ከሂሳብ መደቡ ውጪ በሌላ የሂሳብ መደብ የተመዘገበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

6. <u>በጀት ሳይፈቀድና የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ለጉልበት ሰራተኛ የተፈጸመ ክፍያ</u>

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 የመንግስት መስርያ ቤቶች በጀት ክፍያ የሚፈፀመዉ ወይም ወጪ የሚደረገዉ የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነዉ፡፡ የዚህን መመሪያ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ የደመወዝና ጥቅማጥቅም ወጪዎች በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

አገልግሎቱ በሂሳብ መደብ 2111104 በጀት በማስፈቀድ ወይም የበጀት ዝውውር በማድረግ የጉልበት ሰራተኛ ክፍያ መፈጸም ሲገባው ያለአግባብ ከሂሳብ መደብ 2241106 ብር 67,835.00 ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

7. <u>ሥራ ላይ ያልዋለ በጀትን በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛ በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆኖም ኤጀንሲው የ2014 የበጀት ዓመት አጠቃቀሙን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ለየፕሮግራሞቹ ከተደለደለው የመደበኛ በጀት ሂሳብ በአግባቡ ስራ ላይ ከዋለው ሂሳብ ጋር ሲነጻጸር በየፕሮግራሙ በተመለከቱት አንዳንድ የወጪ አርዕስቶች ከ10% በላይ ሲታይ፡-

በበጀት ዓመቱ ለአገልግሎት መ/ቤቱ ከተደለደለው መደበኛ በጀት በድምሩ ብር 5,415,393.17 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፤</u>

1. <u>የንብረት አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ንዑስ 5 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግሥት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ ሲያበቃ ወይም አገልግሎት ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ የሚል ሲሆን በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አዲስ የተገዙ እቃዎች እንዲሁም መወገድ እያለባቸው ያልተወገዱ የተለያዩ እቃዎች በአንድ እስቶር ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ UPS የማይሰራ በቁጥር 3 ፤ዴል ኮምፒተር በቁጥር 2፤ፕሪንተር በቁጥር 1 ፤ስካነር በቁጥር 2፤ዲኮደር በቁጥር 1 መወገድ ሰኖርበቸው 2 ያለአገልግሎት በስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፤
- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ኤች ፒ ፕሪንተር በቁጥር 5 ፤ብራዘር ፕሪነተር በቁጥር 4፤ እስካነር በቁጥር 3፤ ሶኒ ቴፕነ ሪከርደር በቁትር 3 ጥገና ተደርጎላቸው ስራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ እቃዎች ያሉ መሆኑ፤
- በቆጠራ ኮሚቴ መስራታቸው ተረጋግጦ ጥቅም ላያ ያልዋሉ በርካታ እቃዎች እንደሶኒ ቲቪ በቁጥር 3፤ ሳምሰግ ቴሌብዥን በቁጥር 1፤ኤች ፒ ሞኒተር በቁጥር 3፤ዴል ሞኒተር በቁጥር 10፤ኤች ፒ ሞኒተር በቁጥር 2፤ ሶኒ ሞኒተር 2፤ፕሮጀክተር በቁጥር 3 የመሳሰሉ በርካታ እቃዎች ያለጥቅም በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

2. <u>የተሽከርካሪዎች አያያዝና ፤አጠባበቅና አወጋገድ በተመለከተ</u> ፤

አገልግሎት መ/ቤቱ የተሽከርካሪ ሥምሪት አያያዝ ፤አጠቃቀምና አወጋገድ በፌደራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ሥምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤

- አራት ተሽከርካሪዎች በብልሽት የቆሙ መሆኑ ማለትም ፤ ታርጋ ቁጥር ኢት 4-00174 ሚስት ቡሽ ጃፓን ስሪት የሆነ መኪናና ፤ ኢት 4-03440 ኒሳን መኪና፤4-20496 ጂሊ አውቶሞቢል እና 4-04676 ቶዮታ ቲካአፕ መኪና መወገድ ሲኖርባቸው ለረጅም ጊዜ ቆመው የሚገኙ መሆኑ፤
- በቁጥር 8 የሚሆኑ ሞተር ሳይክልሎች ጥገና ተደርጎላቸው ስራ ላይ መዋል እየቻሉ በብልሽት ምክንያት በአንድ ክፍል ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል።

3. *መሥሪያ ቤቱን ከለቀቁ ሠራተኞች የሚፈለጉ ቋሚ ንብረቶች በተመለከተ*

የኤጀንሲውን የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ከአገልግሎቱ ከሥራ የለቀቁ ሠራተኛ አቶ ሰለሞን እምሩ የግምጃ ቤት ሠራተኛ ኮድ 4-29680 መኪና ሊብሬ ያላስረከቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

8. ክትትል ኦዲትን በተመለከተ

በ2010፣2011፤2013 በጀት ዓመት ኦዲት ላይ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ተገቢ እርምጃ የተወሰደ መሆኑ ሲጣራ፡-

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች፤

- ብር 6,680.22 ከመ/ቤቱ ውጪ ለሆነ የፋና ብሮድካስቲንግ ሚዲያ ሠራተኛ አለአግባብ የአበል ክፍያ ተፈጽሞ ያልተመለሰ መሆኑ

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች፤

- ያለአግባብ ብር 80,380.00 በብልጫ ወጪ ሆኖ ተከፈለ ውሎ አበል ያልተመለሰ

የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች፤

- በጡረታ ለተገለሉ 5 የመ/ቤቱ ሰራተኞች የተሰጠ የገንዘብ ስጦታ ብር 15,000.00 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 6231 በወጪ የተያዘና ለኤጀንሲው ስፖርተኞች የላብ መተኪያ የተከፈለ አበል ብር 20,625.00 በድምሩ ብር 68,625.00 አለአግባብ የተከፈለ በመሆኑ ተመላሽ እንዲደረግ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ብር 20,375.00 ተመላሽ የተደረገ ቢሆንም ቀሪው ብር 48,250.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፡ በኦዲት ታውቋል፡፡

የህግ ጉዳዮችን በተመለከተ(Compliance Issue)

1. ያለውድድር በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዢ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት

ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ተገልጿል፡፡በተጨማሪም ሰኔ 2002 የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 በአዋጅና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መፈጸም እንዳለባቸው ያዛል፡፡ ስለሆነም የእቃና አገልግሎት ግዥ በመመሪያው መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

በድምር ብር 3,314,046.12ያለውድድር በቀጥታ ግዥ በማከናወን ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2. <u>በግዥ እቅዱ መሰረት በጨረታ መከናወን ሲኖርበትበዋጋ ማወዳደርያ የተፈፀመ ግዥ</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሀምሌ 2002 ያወጣው የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም ማንዋል ተራ ቁ. 3.1.1 በእያንዳንዱ የበጀት አመት መጀመሪያ ላይ ሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች ለካፒታል በጀት እና ለመደበኛ በጀት የተሻሻለውን የዓመት እቅድ በሚያንጸባረቅ መልኩ እቅዶችን ማዘጋጀት አለባቸው ፤ የመንግስት መ/ቤቱ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በተሰጠው ፎርማት መሰረት እቅዱን ማዘጋጀት አለበት፡፡ ቅጹ እንደ አግባብነቱ፡- የእቃው ክፍል /የውል ቁጥርን ጨምሮ፣ የግዥው አላማ አጭር መግለጫ፣ ብዛት፣ የጥቅሉ ግምታዊ ዋጋ፣ የግዥ ዘዴ እና የእያንዳንዱ ጥቅል ማስረከቢያ /ማጠናቀቂያ ቀን ማካተት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሀ መሰረት በበጀት አመቱ አገልግሎቱ የፈጸማቸው ግዥዎች በመመሪያውና በእቅዱ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡-

የ2014 በጀት ዓመት የግዥ ዕቅድ ላይ የቋሚና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ግዥዎች በግልጽ ጨረታ እንደሚከናወን ቢገልጽም ከእቅድና ከመመሪያ ውጪ በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ ግዥ በማከናወን በድምር ብር 2,317,165.49 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

3. <u>በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ

በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ የአገልግሎቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ መወራረዱ ኦዲት ሲደረግ፡- በተለያዩ የተሰብሳቢ የሂሳብ ኮዶች (መደቦች)፡በድምሩ ብር 19,193.01 ሳይወራረዱ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡

4. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ፤</u>

የፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ 5 የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ በፊደል (ሐ) የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብርና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡አገልግሎት መ/ቤቱ በመመሪያው መሰረት መፈጸሙ ኦዲት ሲደረግ፤-

በድምሩ ብር 1,557,155.02 በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ በሂሳብ የሚታይ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት